# የተወደደችውን የጌታን ዓመት እንስበክ

ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ
nigatuasteraye@yahoo.com

መስከረም ፩፬ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

*(በኢትዮጵያ አገራችን ለዘመን መለወጫ የሚሰጠው የ"እንኳን አደረሳችሁ" አመጣጥና የያዘው ጽንሰ ሐሳብ::- የተወደደችውን የጌታን ዓመት መስበክ ነው::)*

"ለድሆች ወንጌልን (የነጻነት ምሥራች አዋጅ) እሰብክ ዘንድ ለታሰሩትም መፈታትን፥ ለእውሮችም ማየትን፥ የተጠቁትንም ነጻነት አወጣ ዘንድ የተወደደችውን የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል" (ሉቃስ ፬:፲፰)::

የ፪ሺህ ፫ ዘመናችን ተጠሪ የሆነው ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ከጻፈው ወንጌል የጠቀስኩት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተልእኮየ ነው ብሎ ያነበበው ነው:: ቅዱስ ሉቃስ የጻፈው ይህን የጌታችንን አዋጅ ብቻ አይደለም:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባቶች የየእለቱ መመሪያችን አድርገን እንድንጠቀምባቸው የቅድስት ድንግል ማርያምን አዋጅና፥ የታላቁን ሰው የስሞንን ምኞት በጸሎት መልክ ሰርተው የሰጡንንም የጻፈው እሱ ነው:: ቅዱስ ሉቃስ በወንጌሉ የመዘገባቸው አባቶች ያወረሱን ለየኢትዮጵያዊነት ስነ ልቡና፥ ለመንፈስ ልዕልናና ነጻነት እንዴት መሠረት እንዳደረጓቸው ለማሳየት ያዘጋጀኋትን ዓመታዊት ጦማር እደመድማለሁ::

ጌታችን መድኃኒታችን በእመቤታች ማሕጸን ሰባዊ ባሕርይን ተዋሕዶ ሳለ፥ ወደ መሬት የመጣበትን ምክንያት፥ እናቱ እመቤታችን እንዲህ ብላ ለትውልዱ ሁሉ እንድታውጀው አደረጋት:: ይህ አዋጅ፥ "ለኔ ታላቅ ሥራ አድርጓልኛል::" በማለት ለራሷ ያደረገላትን ከገለጸች በኋላ፥ "በክንዱ ኃይል አድርጓል፥ ትዕቢተኞችን በልባቸው አሳብ በትኗል፥ ኀያሮችን ከዙፋናቸው አውርዷል፥ ትሑታንን ከፍ አድርጓል፥ የተራቡትን ከበረከቱ አጠገባቸው፥ ባለጠጎችንም ባዶአቸውን ሰዷቸዋል፥ ለአባታችን ለአብርሃንም እንደተናገረ ለዘሩ የዘላለም ምሕረቱን አስቦ እስረኤልን ብላቴናውን ረድቷል (ሉቃ ፩:፶፩-፶፬)::" ብላ ለትውልድ ሁሉ የተናገረቸው ነው:: ይህ አዋጅ በመለኮቱ ከአብርሃም በፊት የነበረው የልጇ ቢሆንም፥ በማሕጸኗ ሳለ በእናቱ በቅድስት ድንግል አንደበት እንዲገለጽ ማድረጉ፥ የዘላለም ደሕንነት በመለኮታዊና በሰባዊ ውሕደት እንደፈጸመ ሁሉ፥ ምድራዊ ነጻነትና ሰባዊ ልዕልናም በሰባዊ መንፈስና ሥጋ ውሕደት የሚገለጹ መሆናቸውን ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ይናገራሉ::

ከናቱ ከእመቤታችን በፊት የነበሩ ነብያት፥ በጭቆና ውስጥ ሆነው ነጻ የሚአወጣን አጣን በማለት ወደ ፈጣሪያቸው "ፈኑ ኃይለከ ወንአ አድኅነነ" እያሉ ይጮሁ ነበር:: ይመኙና ይጸልዩም ነበር:: የቀደሙ አባቶች ተሰፋና ጸሎት መፈጸሙን እመቤታችን አወጀችው:: ለእመቤታችን አዋጅ እንጅ ጸሎት አልነበረም:: ይሁን እንጅ አባቶች "ጸሎተ ማርያም" ብለው በምክንያት ሰይመውታል::

ሌላው ስምዖን የተባለው ታላቅ ሰው የተናገረው ነው:: ስምዖን የተናገረው ቃል እንዲህ የሚል ነው:: "አሁን የተመኘሁትን አይቻለሁና ባሪያህን በሰላም አሰናብተኝ" (ሉቃስ ፪:፳፱) ብሎ ወደፈጣሪው ጮኸ:: በጨለማ የነበረው ሕዝብ ብርሃን ወጥቶለት፥ በብርሃንና በክብር ሲመላለስ አይቶ ለማለፍ ፍጹም ምኞት የነበረው ሰው ነው:: የስምዖን ምኞት እንደ ዘመናችን አባቶች ቪላ ቤት ሰርቶ መኖርና የራሱን ሐውልት ማነጽ አልነበረም:: ሕዝባዊ ምኞት ነበረና፥ የተመኘውን ካየ በኋላ የዚህ ዓለም ኑሮ

በቃኝ አለ:: አባቶቻችን የእመቤታችንን አዋጅ ጸሎተ ማርያም ብለው እንደሰየሙት፥ የስሞንንም ርሕራሄ የተመላ ሰባዊ ምኞት፥ የኛም ምኞታችን ሕዝባዊ ይሆን ዘንድ "ጸሎተ ስምዖን ነቢይ" ብለው በመሰየም የዝወትር ጸሎታችን እንዲሆን አደረጉት::

በየአመቱ "እንኳን አደረሳችሁ" እያልን የምንለዋወጠው አመታዊ የምሥራች ቃል ይህን ከላይ የጠቀስኩትን፥ የጌታችንን የእመቤታችንን እና የስሞንን ምኞት ተንተርሶ የተሰራ የተቀደሰ ባሕል ነው:: ይህ የምሥራች ከቡራኬ ጋር ለሕዝብ የሚአቀርበው "እናንተ በልባችን የተጻፉችሁት በሕያው እግዚአብሔር መንፈስ እንጂ በቀለም አይደለም:: ሥጋ በሆነ ልብ ጽላት በድንጋይ ጽላት ያልተጻፈ በእኛም የተገለገለ የክርስቶስ መልእክት እንደሆናችሁ የተገለጠ ነው:: (፪ኛ ቆሮ ፪:፪:፫) ሲል ቅዱስ ጳውሎስ የተናገረውን ቃል ደፍሮ መናገር የሚችል፥ ተቀባዩ ሕዝብም አዎ ልክነው ብሎ የሚአረጋግጥለት የመንፈስና የአዕምሮ ልዕልና የተወሐደለት ቅዱስ የሚባለው አባት ነው::

ይህ ቅዱስ አባት የምሥራች ቃሉ ባዶ ዝናም የሌለው ደመና እንዳይሆን፥ ከዚያ በፊት የሚአደርጋቸው ነገሮች አሉ:: ሉቃስ የተናገረውን ለመፈጸም "ብታሰር፥ ብታመም፥ እንግዳ ብሆን፥ ብታረዝ፥ ብራብ ብጠማ አላደረጋችሁልኝም" ከሚለው መለኮታዊ ወቀሳ ለመዳን ያለውን ኃይል ይጠቀማል:: በሕዝብ ላይ የሚደርሰውን መከራ ሥቃይ ለማቀለል ብቁ ነኝ ብሎ የተሰለፈውን መንግስት፥ ያሰረውን እንዲፈታ ይመክራል፥ ይገስጻል:: ያለምንም በደል እንደታሰሩት፥ የጡታቸው ወትት በደረታቸው የሚሰባቸውን እንደነ ብርቱካን ያሉትን ወጣት እናቶችን ይቅርና፥ ወንጀል የፈጸሙትን እንኳ ቢሆኑ በምሕረት እንዲፈቱ ያደርጋል::

ሃይማኖቱን አክብሮ ያስከበረ፥ አምላክን ወድዶ ያስወደደ፥ በሕዝባዊ ፍቅር ልቡ የነደደ ይህ ቅዱስ ተብሎ የተሰየመ አባት፥ የምሕረት ምንጭ በሆነው አምላክ ስም በሚአቀርበው የምሥራች ቃል ዘመኑን ባርኮ፥ ለሥጋውያን መሪወች አውደ ምሕረቱን ይለቅ ነበር::

መንግሥትም ይህን ቡራኬ በመከተል፥ "ነፍስ አጥፍተው፥ ዘርፈው፥ ቤት አቃጥለው የተፈረደባቸውን በግማሽ፥ በመንግሥት ክብረ ነክ የተፈረደባቸውን በነጻ ተፈተዋል:: ለድሐው ካምናው የሸክም ክብደት ይህን ይህን አቃለናል:: ቀረጥና ግብር ምረናል፥ አስተዳደራችንን በመቃወም የታሰረውን ሁሉ ያለምንም ገደብ ፈተናል:: በዱር በገደል በከተማ ያለውን ሁሉ ምረናል" የሚለውን ይዞ ወደ ሚያገለግለው ሕዝብ አደግድጎ በመቅረብ ለዚህች ሸክም ላቃለልንባት፥ ምሕረትና ይቅርታ ላወንጅበት አመት እንኳን አደረሳችሁ? ይል ነበር::

ሕዝቡም መንግሥት አደግድጎና አክብሮ ያቀረበውን የምሥራች ቃል ባዶ ሐሰት አደንዛዥና አፍዛዥ አዚም ያዘለ እንዳልሆነ ያላንዳች ጥርጥር አምኖ፥ በሕዝባዊ ፍቅር የተቃጠለው መንፈሳዊ አባቱ የመሰከረለት መንግሥት አክብሮ ያቀረበለትን የአዋጅ ገጸ በረከት በመቀበል እርስ በርሱ "እንኳን አደረሳችሁ" ይባባላል:: ይህ ሥርአት ሰው ሰራሽ አይደለም:: የተሰራው ዘንድሮ የተቀበልነው ዘመን የሚጠራባት ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ከመዘገበው ወንጌል "የጌታ መንፈስ በኔ ላይ ነው:: ለድሆች ወንጌልን (የነጻነት ምሥራች አዋጅ) እሰብክ ዘንድ ለታሰሩትም መፈታትን፥ ለእውሮችም ማየትን፥ የተጠቁትም ነጻነት አወጣ ዘንድ የተወደደችውን የጌታን አመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል (ሉቃ ፬:፲፱) የሚልውን መሠረት በማድረግ የተሠራ ቅዱስ ባሕል ነበር::

ይሁን እንጅ ክርስቶስ "የማያዩ እንዲያዩ የሚያዩም እንዲታወሩ: እኔ ወደዚህ ዓለም ለፍርድ መጣሁ"(ዮሐ ፲:፴፱) እንዳለው፥ ይህች ዓለም ዘላለማዊ ነጻነት የማናገኝበት የጨለማው ገዥ ዲያብሎስ በሠራዊቱ አማካይነት ንጹሐን ሰዎች የሚፋለምባት መስክ ስለሆነች፥ የዲያብሎስ ሠራዊቶች እያዩ በጥቅም በራስ ክብርና ኃጢአት አይነ ልቦናቸው ተሸፍኖ ማየት የማይችሉባት፥ የማየትና የማስተዋል ናፍቆትና ፍላጎት ያላቸው እንደ ስምዖን ያሉ ንጹሐን አበው ደግሞ በፍጹም ማስተዋል የሚመላለሱባት መሆኗን የተረዱ ኢትዮጵያውን አባቶች፥ የእመቤታችን አዋጅ ማንም የተጠመቀ ሁሉ በልቡ እንዲጽፈውና በየቀኑ እንዲደግመው በጸሎት መልክ ሠሩ:: ይህ በእመቤታችን አንደበት የተገለጸው አዋጅ ሲሆን አባቶች "ጸሎተ ማርያም" ብለውታል::

እነ ዶክተር Mbiti ስለ ቤተ ክርሲያናችን ሲጽፉ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን " a big place given to the Blessed Virgin Mary," ማለትም:- የኢዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለድንግል ማርያም ከፍኛ ቦታ ትሰጣለች እያሉ የጻፉት፥ በዚህ ግንዛቤ እንጅ ከሮማን ካቶሊኮች ነገረ መለኮት ጋራ በተያያዘ ዛሬ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ስም ለመነገድ እንደሚሰበከው አልነበረም::

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የተናገረውን እጠቅሳለሁ:: እንደዘመናችን ያሉ መሪዎች ገጠመውና ለተመልካች እንዲህ አለ:: "ርኢከኑ ከመ ኃጢአት ትሬስዮ ለሰብእ ጽኑአ ልብ እንበለ ሃይማኖት ወዘእንበለ ፍርሃት ወዘእንበለ ሰላም እንዘ ይብል አልቦ እግዚአብሔር" (ሃይ አው ፷፬:፳) ማለትም:- ለመሆኑ ኃጢአት ሰውን እግዚአብሄርን የማይፈራና ሰውን የማያፍር ሰላም የለሽ እንዴት እንደሚያደርገው ትመለከታለህን? አለ:: ይህ ሊቅ ቀጠለና ይህን ሲአብራራ "እስመ እምጽንአተ ልብ ይከውን ተቃርኖተ ሃይማኖት: ወበከመ ሥጋ ዘየአኪ ደዌሁ ኢይትወከፍ ፈውሰ ከማሁ ነፍስሂ እንተ ኢትፈርሆ ለእዚአብሔር ኢትጥእሞ ግሙራ ለቃለ እግዚአብሔር በእንተ ጽንአተ ልባ ዘንተ ከመ ኢንኩን ዘከመ ኢምእመናን::" (፷፬ :፲፪) አለ:: ማለትም:- ሰው መንፈሰ እግዚአብሔር ከተለየው ሃይማኖትን እውነትን ሰባዊ ነጻነትን ይቃረናል:: የልብ ድንዳኔውም ለማይፈወስ አደጋ ያግልጠዋል::

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ጥቆማ በመጠቀም የዘመናችንን ፐትርያርክ ካለፉት ከነ አቡነ ባስልዮስ ጋራ እስቲ እናነጻጽራቸው:: ቅዱስ አባታችን አቡነ ባስልዮስ እሳቸው ካለፉ በኋላ ለሚመጣው ትውልድ ከማሰባቸው የተነሳ፥ ሕዝቡ ከሃይማኖቱ እንዳይናወጽ በማሰብ "የተዋሕዶ ሃይማኖት ነገረ መለኮት የተቀረጸበትን ሃይማኖተ አበው የሚባለውን ታላቁን መጽሐፍ አዘጋጅተው ለየደብሩ እንዲሰራጭ ሲያደርጉ "ኢትዮጵያዊ ሁሉ እንከን ያልተቃላቀለበትን የእምነቱን ትምህርት አጽንቶ ጠብቆ ይኖርበታል ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም ለዓላማዋ ማስከበሪያ ለጠላቶቿ ማሳፈሪያ ይሆናል ብለን ተስፋ እንደርጋለን" ሲሉ የተናገሩት የኑዛዜና ያደራ ቃል የበለጠ ቅዱስ ያደርጋቸዋል::

የዛሬው ፓትርያርክ ቤተ ክርስቲያኗን ልግል ክብራቸውና አላማ መሣሪያ ለማድረግ ጎልቶ በሚታየው ፍላጎታቸው፥ የብሉዩና የሐዲሱ ማብራሪያ ከሆነው የቤታችንን መሠረታዊ የነገረ መለከቶ ትርጉም ከያዘው ጋር የሚቃረን፥ ቤተ ክርስቲያናችንን ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነቷና ትምህርቷ የሚያናጋ የዘጠኝ መለኮት ትምህርት አራማጆች መጽሀፍ ሲቀርብላቸው በደስታ እየተቀበሉ እንዲሰራጭ የሚተባበሩ ናቸው::

የቀደሙ አባቶች ያለባቸውን ሃይማኖታዊ ሐላፊነት ለመወጣት ክርስቶስ በወንጌሉ የሰጠውን ማስጠንቀቂያ በመገንዘብ፥ ያሰራችሁትን ፍቱ እያሉ መንግሥትን በመጠየቅ የይቅርታ አዋጅ እንዲታወጅ ያስደርጉ ነበር:: ተቀባይ ሲያጡ፥ እኔንም ጨምራችሁ እሰሩኝ ይሉ ነበር:: ይህንም የሚቀበላቸው ሲአጡ፥ ጥያቄያቸው መልስ እስኪአገኝ ድረስ ቤታቸውን ዘግተው አትቅረቡኝ ይሉ ነበር:: ተመሳሳይ እምነት ያላቸው እንደ አቡነ ሽኖዳ ያሉት ኦርቶዶክሳውያን አባቶች፥ ዛሬ በሚሊዮን የሚቆጠረው አማኞች ወገኖቻችን የሚደርሰው መከራና ሥቃይ ይቅርና ባንዲ ኦርቶዶክሳዊት ምእመን ላይ ግልምጫና ንቀት ሲደርስ ይህን ለማስቆም ኃላፊነት ካለበት መንግሥት ጋራ መብላትና መጠጣት ይቅርና፥ ለዓለም ሁሉ ያጋልጡታል፥ ይተናነቁታል:: ጥያቄያቸው ተመልሶ የታሰረች አካል እስክትፈታ ድረስ መንበራቸውን ጥለው ወደበርሐ ይሄዳሉ::

በሃይማኖት አንጻርም በኛ ቤተ ክርስቲያን እንደሚታየው በዘጠኝ መለኮት ትምህርት ያደገ ሰው በሚጽፈው በሚለቀልቀው ኩርባብች የተዋሕዶ አዕማድ የሚባሉትን አበው እየነቀፈና እምነቱን እያፋለሰ ህዝባቸውን እንዲበክል ሊፈቅዱ ቀርቶ፥ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት በተናጋበት እንደ ከንሳስ ባሉ ቦታዎች ሁሉ በመገኘት ቀጥተኛውን ትምህርት እየመሰከሩ ናቸው:: እንደዘመናችን ፓትርያርክ በቁማቸው የድንጋይ ሐውልት አሠርተው ከድንጋይ ጋራ የሚጫወቱና የሚደንሱ አይደሉም::

አቡነ ጳውሎስ ከእምነቱ ጋራ ከመጋጨታቸውም በላይ፥ የገንዘብና የፖለቲካ ትርፍ የሚአሳድዱ በመሆናቸው የማይታዘዛቸውን ለመጉዳት የተቀደሰውን ነገረ

መለኮት ሳይቀር እንደጥይት እንደተጠቀሙበት ደጋግመው በፈጸሙት ደባ ተረጋግጧል:: "ትርፍ ለማግኘት የሚሳሳ ሰው የራሱን ቤት ያውካል"(ምሳ ፲፭:፳፯) የተባለው በራሳቸው ተተረጎመባቸው:: በእግዚአብሔር ቤት ሆኖ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት መጣር ይቅርና፥ ትርፍ ለማግኘት አላማ ያላቸው ነጋዴዎች እንኳ፥ ያለአግባብ ለማትረፍ ከጨቃኝ መንሥት ጋራ በመተባበር ሕዝቡን ሲዘርፉ "ኃላፊነት ከጎደለው ነገ ከዙፋኑ ከሚገለበጠው መንግሥት የተጠጋችሁት፥ ይህ የተጠጋችሁት መንግሥት ሲወድቅ እናንተም ከሰበሰባችሁት ንብረታችሁ ጋር ትበተናላች" ብላለች ብለው የእመቤታችንን አዋጅ መናገር በተገባቸው ነበር:: ግን እሳቸውና የሰየሟቸው ጳጳሳት ከስግብግብ አትራፊወች ብሰው ሕዝቡን እነሱም እየዘረፉ በማዘረፍ ላይ ናቸው::

በቤተክርስቲያናችን ውስጥ በምሥጢርና በገሀድ የሰበሰቧቸው ግማሾቹ በዘረፋ የተዘፈቁ፥ ሌሎቹ በዘጠኝ መለኮት እምነታቸው ከደብረ ሊባኖስ ገዳም ከተባረሩ ሰው ተማርን እያሉ፥ የጉባዔ ሊቃውንት ካስተማሩን ውጭ የሆነ ክህደትና ቤተ ክርስቲያናችንን የሚአስነቅፍ ኩርባብቻቸው፥ (ተራ ነገረ ዘርቅ አሉባልታና የግል ጥላች የተመላበት መጽሐፍ) ቀጥተኛውን እምነትና ትምህርት እየዘበራረቁ በሽያጭ በማቅረብ ሕዝቡን ገንዘቡንም ስነ ልቡናውንም በማዘረፍና በመዝረፍ ጥረታቸውን እንደቀጠሉ ናቸው::

"ወኢትንስት ደወለ ገራህት ዘአንበሩ አበዊከ ዘለዓለም(ምሳ ፳፫:፲) አባትና እናትህ የሰሩልህን ዳር ድንበር አታፍርስ የሚለው ሕግ ሲጣስ በዝምታ የምትተበባሩ፥ "ወበዕለተ ምንዳቤ እስከ የኃልቅ አድኅን እለ ይስሐቡ ውስተ ሞት"(፳፬:፲፩) ወደ ሞት የሚነዱትን ታደግ:: ሊታረዱ የተወሰዱትን አድን:: ይህን አላውቅም ብትል ልቦችን የሚመረምር እርሱ አያስተውልምን? ነፍስንስ የሚመለከት እርሱ አያውቅንም? ለሰውስ ሁሉ እንደሥራው አይመልስለትምን? (ምሳ ፳፬:፲፩.፲፪) በሚለው ቃል እራሳቸውን የማይመዝኑና የማያስተካክሉ ኃላፊነት የማይሰማቸው፥ ጨካኞች ናቸው:: "እንኳን ለዘመነ ሉቃስ አደረሳችሁ" ማለት ይቅርና ለመጎራበትም የበቁ አይደሉም::

ብዙዎቹ በተለይም በዲሱ ዘሩያ ያሉት አስመሳይ ካህናት ነን ባዮች፥ ከራሳቸው ሐውልት ጋር ለሚደንሱት ለአቡነ ጳውሎስ ምልእክተኞች በመሆን፥ ሹመት ገንዘብ ለማግኘት በሚያደርጉት ጥረት፥ ገለልተኛ ነኝ ከሚለው ሕዝብ እየተደበቁ በሚፈጽሙት ደባ፥ ያቡነ ጳውሎስን እኩይ አላማ የሚቃወመውን ሁሉ በቀላማጅ አንደበታቸውና ኑፋቄ በተመላው ኩርባብቻቸው ስብከታቸውን ቀጥለዋል:: በዚህ እኩይ አላማ ውስጥ ገብተን እንድንተባበር ለማድረግ እየጣሩ ናቸው::

የሚበላ የሚጠጣ የሚንቀሳቀስ ሰው በእምነት በአገር በሕዝብ ላይ ከሚደርሰው ችግር ሁሉ ገለልተኛ ነኝ ማለት፥ እሬሳ ነኝ ማለት ነው:: ከመብልና ከመጠጥ ሳይገለል፥ "ገለልተኛ ነኝ" ማለት ማትልያና ማጭበርበሪያ ቃል ነው:: ሃይማኖት ፈረሰ ድንበር ፈረሰ፥ የሰው ክብር ተገሠሠ፥ ማለትና ይህን ሁሉ የሚፈጽሙ ሁሉ ይዋረዱ ይውደቁ አልልም ማለት፥ የጸሎተ ማርያምን ትርጉም አለማወቅ፥ እንደ ስሞን ለሕዝብ ቅድሚያ ከመስጠት ይልቅ፥ ለሆድ ስፋት፥ ለደንደስ ስባት ቅድሚያ መስጠት መሆኑን ልናስተምራቸው የሞራል ግዴታ አለብን::

ዛሬ በታሪክ የተነገረውንና በቅዱስ መጽሐፍ የተገለጸውን እኛነታችንን እንድንረሳ የተዘመተብን የፍዳ የመከራና የሥቃይ ዘመን ነው:: ይህን የፍዳ ዘመን በማራዘም ላይ ያሉት የእመቤታችንን አዋጅ ሳይረዱ፥ የስሞንን ምኞት ሳንገነዘቡ፥ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመግባት ባጥንቱ ከቆመው ሕዝብ እየተገፈፈ፥ ወደሙስና ሰዎች የሚጎርፈውን ገንዘብ ለመሻማት በሚአስችላቸው መንታ መንገድ ላይ የቆሙ፥ ጨርሰውም የተዘፈቁ፥ ካህናትና ሰባኪዎች ናቸው::

በኢትዮጵያ አገራችን "እንኳን አደረሳችሁ" የሚል መንፈሳዊ መሪ እንደሌለ በቋንቋና በስሜት የምንግባባ እኛ እንቅርና ዓለም አውቆታል:: ምእመናኑ የሚለብሰውና የሚጎርሰው አጥቶ እየተሠቃየ፥ የወለደውን ልጅ ወደማያውቀ አገር እንዲሄድለት እየታገለ ባለበት ወቅት፥ መነኩሴና መናኝ ንኝ የሚሉት አቡነ ጳውሎስና የሰበሰቧቸው መነን መነኮስን፥ ሞትን የሚሉ ሰዎች ግን፥ ቤተ ክርስቲያናችንን ወፍረው ሊፈነዱ የደረሱባት፥

በሚመጡት ቅልጥም፥ በሚጠጡት ውስኪ ግፌት ጥጋብና ሥካር እርስ በርሱ የሚደባ ደቡባት ያምባጓሮ ከተማ አድርገዋተል::

ስለ ቤተ ክርስቲያናችን አስደናቂ የሕይወት ታሪካዊ ጉዟዋ አድንቀው የጻፉ Mbiti የተባሉት ሊቅ "Which partly helped it to aquire a uniquely African expression," እንዳሉት፥ ቤተ ክርስቲያናችን ይህን የመሰለ ክፉ ዘመን ሲገጥማት ብሶቷን ለሕዝባ የምትገልጽባቸው ልዩ፥ ብዙ ቋንቋና ጠባይ አሏት:: ከነዚህ አንዱ "እማእሰረ ኃጢአት እግዚአብሄር ይፍታህ" የምትለው ሐረግ ናት:: ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን መንበር ላይ የተቀመጡት መንፈሳዊ ነኝ የሚሉ ሰው ሕዝቡን በሕይወቱ የቀበሩና ይህንም መቃብር ለሕዝቡ ሲመኙ የኖሩ ናቸው ቢባል ከእውነት መራቅ አይደለም:: የኢትዮጵያን ሕዝብ "እንኳን አደረሰህ" ማለት የማይችሉ እራሳቸው በኃጢአት ሰንሰለት ታስረው የኢትዮጵያን ሕዝብ ላሳሪ አሳልፈው የሰጡ ናቸው::

ዛሬ በባላገር ያለው አንጎራጓሪው ሁሉ "ያንበሳውን ጋማ አሕያ ነጨችው፥
ያንበሳውን እግር ውሻ ነከሰችው፥
ዓለም ጉደኛ ናት ይህን አሳየችው"

እያለ በሕዝቡና በነአቡነ ጳውሎስ መካከል ያለውን ምሬታን ንቀት በማንጎራጎር መልእክቱን እያስተላለፈ ነው:: ታዲያ የእኛ የካህናቱ መልክት ምንድነው? የማን መልእክተኞች ነን? ተልእኳችንስ ወዴት ነው? የዘመኑ ባለቤት ቅዱስ ሉቃስ ያሰፈረውን "ገዥዎችን ከዙፋናቸው አውርዷል፥ ትሑታንን ከፍ አድርጓል፥ የተራቡትን ከበረከቱ አጠገባቸው፥ ባለጠጎችንም ባዶአቸውን ሰዷቸዋል፥" የሚለውን የእመቤታችን አዋጅ፥ አባቶቻችን ሠረተው በዝወትር ጸሎት መልክ እንድንደግመው ያዘዙን እኮ፥ ለልማድ እንደሚታኘክ ማስቲካ ባፋችን ለማልጎምጎም አይደለም:: ይህን በመሰለ ወቅት ካንደበታችን አውጥተን ያላንዳች ውልውል እንድናውጀው ነበር:: ልጇ ጌታችን ክርስቶስም "ለድሆች ወንጌልን (የነጻነት ምሥራች አዋጅ) እሰብክ ዘንድ ለታሰሩትም መፈታትን፥ ለእውሮችም ማየትን፥ የተጠቁትንም ነጻነት አወጣ ዘንድ የተወደደችውን የጌታን አመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል" እንዳለውም ሕዝቡ የሚናፍቀውንና የተጠማውን በጌታም በህዝብም የተወደውን የምሕረትን አመት እንድንሰብክ እንጅ በአቡነ ጳውሎስ በኩል የሚለፈፈውን የዚህን ክፉ ዘመን ርዝመት ለማስተጋባት አይደለም::

ባንደበታቸውና በኩርባብቻቸው እኛን ለመከፋፈልና ለመለያየት የሚጥሩትን የአቡነ ጳውሎስን ጅራቶች ሁላችንም ተባብረን "ጸሎተ ማርያም" የማትደግሙ ከቤተ ክርስቲያናችን ስነልቡና የወጣችሁ ናችሁ! ብለን በማባረር ያቡነ ጳውሎስን ክንድ ማሳጠር የሞራል የመንፈስና የታሪክ ግዴታ አለብን:: የዚህ ዘመን መርሐ ግብራችን በዚህ ላይ የተመሠረተ ቢሆን፥ በሕዝባችን ላይ ለመፈጸም የታቀደውን ረዥም የመከራ ዘመን ከሚአሳጥሩት መፍትሔዎች አንዱ ሊሆን የሚችል ይመስለኛል::

የምሕረት አምላክ እግዚአብሔር ለታሰሩ መፈታትን፥ ለተጠቁት ነጻነትን፥ ለመስበክ የእመቤታችንን አዋጅ፥ የስምዖንን ስሜት በልቡናችን ያሳድር::

ይቆየን

ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ

*ለሌሎች የቂሲስ አስተራየ ጽጌ ጦማሮች የሚከተለውን ድህረ-ገጽ ይመልከቱ፥*
***http://www.medhanialemeotcks.org/***